# ሞጁል ሰባት

# የቴምብር ቀረጥ አስተዳደር ሥልጠና ሞጁል 7 ሞጁል

# መግቢያ

የቴምብር ቀረጥ በሰነዶች ላይ የሚጣል ቀረጥ ሲሆን እንደ ማንኛውም ታክስ መንግስት ለጠቅላላው ህብረተሰብ ጥቅም የሚያወጣቸውን ወጪዎች ለመሸፈን እንዲችል ታክስ ከፋዮች ያለ ምንም ቀጥታ ጥቅም የማግኘት ጥያቄ መክፈል ያለበት በህግ የተጣለ ግዴታ ነው ::

የቴምብር ቀረጥ በጽሑፍ በሚደረጉና ለአድራጊዎቻቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኙ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ህጋዊ እውቅና ወይም ማረጋገጫ በሚሹ ሰነዶች ላይ በሰነዶቹ ተጠቃሚ በሆኑት ወገኖች ላይ ቀረጥ በመጣል ገቢ የሚሰበሰብበት ቀጥተኛ ካልሆኑት የታክስ ዓይነት ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ቀረጡ የሚጣለውና የሚሰበሰብበት ሰነድ መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት ፤የተመዘገበበት ፤የተላለፈበት ፤የተወገደበት፤ ልኩ የተወሰነበት ወይም የተስፋፋበት ወይም በሰነዱ በጽሑፍ የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የሚባልበት ማንኛውም በጽሑፍ በተዘጋጀ ሰነድ ነው፡፡

የቴምብር ቀረጥ በጽሑፍ ባልተደረገ ወይም በቃል በተደረገ መብት ወይም ግዴታ የሚፈጥር፤ነባሩን የሚያሻሽል ወይም በሚያስቀር የውል ስምምነት ላይ ሊጣልና ሊሠበሰብ አይችልም፡፡

የቴምብር ቀረጥ የሚጣለውና የሚሰበሰበው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መብት እና ግዴታ የተቋቋመባቸው፤የተሻሻለባቸው ፤የተቋረጠባቸው፤ ቀሪ የተደረገባቸው ወይም የግዴታ መፈጸም በሚጠየቅባቸው በጽሑፍ በተዘጋጁ ሰነዶች ላይ በመሆኑ ቀረጡ እንደሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች **በግብይት ላይ የሚጣል ታክስ አይደለም** ፡፡ ሌላው የቴምብር ቀረጥን ከሌሎች ታክሶች የሚለየው ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው **ለቴምብር ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ** ግዴታ የለበትም ፡፡

በኢትዮጵያ የቴምብር ቀረጥ የሚጣለውና የሚሰበሰበው በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 ፤ የአዋጁ ማሻሻያ ቁጥር 612/2001 እና በቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954 ቢሆንም የደንቡ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከአዋጅ ቁጥር 110/1990 እስካልተቃረኑ ድረስ ብቻ ነው፡፡
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 96(7) የቴምብር ቀረጥ ሽያጭ ፣ ቀረጡን መጣል እና መሰብሰብ ሥልጣን የፌደራል መንግስት እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ ለክልሎች በአስተዳደር ወሰናቸው ለሚያከናወኑ ሰነዶች የሚያስከፍሉት የቴምብር ቀረጥ በግልጽ አልተወሰነም ነበር ፡፡
በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መስከረም 25 ቀን 1996 ዓ.ም በጋራ በወሰኑት መሠረት የቴምብር ሽያጭ/ቀረጥን በተመለከተ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 96 የቴምብር ቀረጥ እንደሚጥልና እንደሚሰበስብ የተደነገገው ድንጋጌ የክልል መንግስታት የራሳቸውን የቴምብር ቀረጥ መጣል እንደማይችሉ የሚያመለክት ባለመሆኑ እንዲሁም የቴምብር ቀረጥ በሰነዶች ላይ የሚጣል በመሆኑ የክልል መስተዳደሮች በሚያስፈጽሟቸው ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጡን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን እንዲሠጣቸው ተወስኗል ፡፡ በመሆኑም ክልሎች **የቴምብር ቀረጥ ህግ በማውጣት** ከዚህ ቀረጥ ዓይነት ታክስ መሰበሰብ እንደሚቻል ግንዘቤ መያዝ ይቻላል ፡፡

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

## 1.1 ዓላማ

### ➢ ዋና ዓለማ

በቴምብር ቀረጥ ህግ ውስጥ ስለተደነገጉት የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች፤ አተማመን፤አከፋፈል፤የክፍያ ጊዜ እና የቀረጡ አስተዳደር ሥነ ሥርዓቶችን በተገልጋዮች ግንዘቤ እንዲያዝ ማድረግ ሆኖ

### ➢ ዝርዝር ዓላማዎቹ ተገልጋዮች፡

- የቴምብር ቀረጥ ጽንሰ ሃሳብን ይረዳሉ ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ የሚጣልባቸው ሰነዶችን ያውቃሉ ፡፡
- ከቴምብር ቀረጥ ነጻ የሆኑትን ዕቃዎችን / አገልግሎቶችን ይለያሉ ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ ሥሌት መሰረትና መጣኔን ያሰረዳሉ ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ የክፍያ ሁኔታን ይገልጻሉ ፡፡
- የቴምብር ቀረጥን አለመክፈል የሚያስከትለውን አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶችን ይገነዘባሉ፡፡

## 1.2 ውጤት

ተገልጋዮች የቴምብር ቀረጥ ህግ ድንጋጌዎችንና አስተዳደራዊ ሥነሥርዓቶች ላይ ግንዘቤ በመፍጠር መብታቸውን ያስከብራሉ ፤ ግዴታቸውን ይወጣሉ ፡፡

## 1.3.ወሰን

### 1.3.1. ሽፋን

ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል አዋጅ ቁጥር 110/1990፤ የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 612/2001፤ ደንብ ቁጥር 221/1954 እና የፌዴራል ታክስ አስተዳደር
አዋጅ ቁ.983/2008 ያካትታል ፡፡

### 1.3.2.የስልጠናው ተሳታፊዎች

ታክስ ከፋዮች ፤ የንግድ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ፤ የውሎች አስፈጻሚ ተቋማትና ሌሎች ጉዳያቸውን በሰንድ የሚፈጽ / የሚያስፈጽሙ ተገልጋዮች ይሆናሉ ፡፡

### 1.3.3. ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ.፡ ሁለት ሰዓት ይሆናል ፡፡

## 1.4. ትርጓሜ

1.4.1. **ሰነድ ማለት** ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፣ የተላለፈበት፣የተወገደበት፣ ልኩ የተወሰነበት ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም ጹሁፍ ነው ።

1.4.2. **ግልግል** (Award) ማለት ስለ ዕርቅ፣ ስለ ስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሑፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው።

1.4.3. **ማገቻ** (Notarial acts/ bond) ማለት የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጪው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ የሚጨምር ይሆናል።

1.4.4. **በንግድ ህጉ ማገቻ ወይም ቦንድ ማለት** የአክሲዮን ማህበራት ካፒታላቸውን ለማሳደግ የሚያወጧቸው የግዴታ ወረቀቶችን ይጨምራል ።

1.4.5. **የመያዣ ሰነድ** /security deeds/ ማለት ተበዳሪው ወይም ዋሱ ለአበዳሪ በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት የውል ሰነድ ነው ።

1.4.6. **የህብረት ስምምነት** ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ የሠራተኞች ማህበራት ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሠሪዎች ወይም አሠሪ ማህበራት ወኪሎች ወይም አሠሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል **ስለ ሥራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሑፍ የሠፈረ ስምምነት** ነው ።

1.4.7. **የሥራ (የቅጥር) ውል** ማለት ማንኛውም ሰው ደመ-ወዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት ሲስማማ **በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል** ነው።

1.4.8. **ማረጋገጫ** ማለት አዲስ ሰነድ በአዘጋጁ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ሲፈረም ማየትና ይኸው መፈጸሙን በማረጋገጥ በሰነዱ ላይ መፈረምና ማህተም በማድረግ ወይም አስቀድሞ የተፈረመ ሰነድ ላይ የሚገኝ ፊርማና ወይም ማህተምን በቃለ መሃላ ወይም በናሙና ፊርማ ወይም ማህተም ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በሰነዱ ላይ በመፈረም እና ማህተም በማድረግ የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰንድ ነው ።

1.4.9. **ሰነድ ማስፈጸም** ማለት ሰነድ መሥራት፣ማውጣት፣በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው ።

1.4.10. ***የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ*** (warehouse bond) ማለት ሸቀጦችን እየተቀበለ በማከማቻ ሥፍራ እንዲያስቀምጥ ከህዝብ አገልጋይ መሥሪያ ቤት ባለስልጣን ለዚህ ዓይነት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ዕቃ አከማች የተባለ ሰው ይህን ዕቃ የገዛው ወይም በመያዣ የተቀበለው የማከማቻ ዕቃ ሰጭ ተብሎ ለሚጠራው ሰው ጥቅም ዕቃውን ተቀብሎ በማከማቻው ሥፍራ እንዲያስቀምጥለት በውል ግዴታ የሚገባበት ውል (ፍትሓብሔር ህግ አንቀጽ 2806 )

1.4.11. ***መተዳደሪያ ደንብ*** ማለት እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ጹሑፍን የሚጨምር ሰነድ ነው ፡፡

# ክፍል ሁለት

# የቴምብር ቀረጥ አስራር ሥርዓት

## 2.1. የቴምብር ቀረጥ ስለመጣል

የቴምብር ቀረጥ በዋናነት በሰነዶች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ የመንግስት የገቢ ምንጭ ሲሆን ቀረጡን በሰነዶች ላይ በመጣል እና በመሰብሰብ የታክስ ፍትሃዊነት እና የሃብት ክፍፍልን በማመጣጠን የመንግስትን የገቢ ምንጭ ለማስፋት ያግዛል ፡፡ በኢኮኖሚ አውታር ውስጥ በሚፈጠር የዜጎች እንቅስቃሴ የኢኮኖሚ ዋጋ ያላቸውን ሰነዶች የማስረጃነት ተቀባይነትን እንዲጨምር የማድረግ አላማ ያለው ሲሆን በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 መግቢያ ላይ በሰነዶች ላይ የሚጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነ-ጥበብ ዕድገትን፤የፋይናንስ ተቋሞችን እንቅስቃሴ እና የካፒታል ንብረት ዝውውርን የማገዝ አላማ እንዳለው አዋጁ ይገልጻል ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቴምብር ቀረጥ ህግ ገና በማደግ ላይ ባሉ እና ባላደጉ አገራት በንብረት ማስመዝገቢያ (በመኖሪያ ቤት፤በግብርና መካናይዝድ ተሽከርካሪዎች) ላይ፤ በባንክ ብድር መያዣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፤ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ንብረት ለማፍራት በሚወስዱት ብድር መያዣ ላይ ቀረጡ መጣሉ ለመንግስት ከሚያስገኘው ገቢ ይልቅ ኢንቨስትመንትን ያዳክማል፤ዜጎች በብድር ንብረት የማፍራት ፍላጎታቸውን ይቀንሳል በማለት የመከራከሪያ ሃሳብ የሚያነሱ ምሁራን አሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀረጡ የሚከፈለው በሰነድ ላይ በመሆኑ እንዲሁም መንግስት የገቢ ምንጩን ማስፋት መቻሉንና ታክስ የመጣል አላማ ገቢ ከማግኘት ባለፈ በዜጎች መካከል የሃብት ክፍፍልን ለማመጣጠን የታክስ መጣል ትሩፋቶችን በመጥቀስ የቴምብር ቀረጥ በሁሉም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያስገኙ፣ የንብረት ባለቤትነትን በሚያስረዱ እና መብት ወይም ግዴታ መፈጸም በሚጠየቅባቸው ሰነዶች ላይ መጣሉ አስፈላጊ እንደሆነና ነገር ግን የቀረጡን በተወሰኑ የኢኮኖሚ መስኮች፣ በኢንቨስትመንት እና በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያሳርፈውን ጫና ለማመጣጠን በህጉ የነጻ መብቶች ድንጋጌዎች መቀመጣቸው መሰል ጉዳዮችን ለመፍታት ያስችላል ተብሎ ይታመናል ፡፡

በሃገራችን በሥራ ላይ ያለው የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 ከዚህ ቀረጥ ነፃ መብቶችን የያዘ እና በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ከአገራዊ ጥቅም ጋር ተያይዞ በቂ ምክንያት ሲቀርብ በቀረጡ መጣል ተጽእኖ የሚደርስባቸው መስኮችን ነጻ ሊያደርግ የሚችልበት አግባብ በአንቀጽ 11 ተደንግጓል፡፡ ይህም ቀረጡ ይጎዳቸዋል የሚባሉትን የኢኮኖሚ መስኮችም ሆነ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከቀረጡ ነጻ የሚሆኑበት መንገድ በገንዘብ ሚኒስቴር መስፈርት መሠረት የሚወሰንበት አግባብ መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው/ የሚጣልባቸው ሰነዶች

የቴምብር ቀረጥ በሰነዶች ላይ የሚጣል የታክስ ዓይነት ሲሆን ቀረጡ የሚጣለውና የሚሰበሰብበት በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 2(5) ላይ ለሰነድ በተሰጠው ትርጉም መሠረት ነው፡፡

በሌላ በኩል የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸውን ሰነዶች በዝርዝር እና በቴምብር ቀረጥ አዋጁ በዓይነት ተደንግጓል ፡፡ ይህም የተዘረዘሩት ሰነዶች ስለ ሰነድ የተሠጠውን ትርጉም የሚያሟሉ ናቸው ብሎ መውሰድ አግባብ ነው፡፡ ሆኖም በአንቀጽ 3(5) ላይ **የውሎች ስምምነቶችና መግለጫዎችቻቸው** የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች በማለት የተቀመጠው በጥቅሉ በመሆኑ የትኞዎቹ ውሎች፣ ስምምነቶች እና መግለጫዎች በጽሑፍ ሲደረጉ የቴምብር ቀረጥ መከፈል እንዳለበት ለመወሰን የፍትሐብሔር ህጉ ስለ ውሎች አጻጻፍ ፎርም ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1678(ሐ) እና 1719(2) ውሎች በህግ በተለየ ፎርም እንዲደረጉ ካልተደነገገ በስተቀር ለውሎች በህግ መጽናት በጽሑፍ እንዲደረጉ ግዴታ አይጥልም ፡፡

በመሆኑም በህግ በጽሑፍ እንዲደረጉ አስገዳጅ ህግ የተደነገገባቸው ውሎች በጽሑፍ እንዲደረጉና እንዲመዘገቡ አስገዳጅ የህግ ቅድመ ሁኔታ በመኖሩ እነዚህ ውሎች ሲመዘገቡ የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የውሎች ስምምነቶች እና መግለጫዎቻቸው በህግ በጽሑፍ እንዲደረጉ አስገዳጅ የሆነው ህግ የማይመለከታቸው ውሎች በተዋዋዮች ፍቃድ በተለየ ፎርም ወይም በጽሑፍ ማድረግ እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ1719(3) ይገልጻል ፡፡ ሆኖም እነዚህ ውሎች በተዋዋዮች ፈቃድ በጽሑፍ ቢደረጉም እንዲመዘገቡ የሚያስገድድ ህግ ባለመኖሩ የሚመዘገቡ ሰነዶች አይደሉም፡፡ ነገር ግን እነዚህ በጽሑፍ የተደረጉት ውሎች በአዋጁ አንቀጽ 2(5) ስለ ሰነድ የተሠጠውን ትርጉም የሚያሟሉ መብትና ግዴታ የተቋቋመባቸው የውል ሰነዶች ከመሆናቸው አንጻር የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል ወይንስ አይከፈልባቸውም የሚለውን የሚመልስ በአዋጁ የተቀመጠ ግልጽ ድንጋጌ የለም ፡፡ ነገር ግን ከአዋጁ አጠቃላይ አላማ በመነሳት በአዋጁ ተለይተው ባልተጠቀሱ የውል ሰነዶች ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ውሎቹ በህግ በጽሑፍ እንዲደረጉና ለህጋዊ ውጤት በመንግስት አስተዳደር መ/ቤት እንዲመዘገቡ ወይም በውልና ማስረጃ እንዲረጋገጡና እንዲመዘገቡ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ የተጣለባቸው ውሎች ናቸው ፡፡

በመሆኑም በፍትሐብሔር ህግ ከአንቀጽ 1723 እስከ 1725 ድረስ የተዘረዘሩት የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች፣ልዩ ባህሪ ያላቸው የማይንቀሳቀስ ንብረት ውሎች፣ረዥም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች፣የዋስትና ውሎች፣ የኢንሹራንስ ውሎች እና በህግ በጽሑፍ መደረግ ያስፈልጋቸዋል የተባሉ ሌሎች ውሎች የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው የውል ሰነዶች ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 3 ላይ የቴምብር ቀረጥ የሚከፍልባቸው ሰነዶች በዝርዝር ከንዑስ ቁጥር 1 እስከ 12 ድረስ የተዘረዘሩ የሚከተሉት ሰነዶች ናቸው ፡፡

**2.2.1** . የማንኛውም ንግድ ማህበር፤ የህብረት ሥራ ማህበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማህበር መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ፤

**2.2.2** . ግልግል የተፈጸመበት ሰነድ በሚረጋገጥበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ነው፤የቀረጡ አተማመን ስልትም በዋጋው መሠረት የሚከፈል ነው ፡፡

**2.2.3** .**ማገቻ** (bonds)፤ ሰነድ በሚረጋገጥበት ጊዜ እና በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ ይከፈልበታል፡፡ በንግድ ህጉ ማገቻ ወይም ቦንድ የአክሲዮን ማህበራት ካፒታላቸውን ለማሳደግ የሚያወጧቸው የግዴታ ወረቀቶችን ይጨምራል ፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ወይም የውል ማስከበሪያ የሚጠይቅ ሰው ዋስትናውን የሚሠጠው በሰነድ ከሆነ በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር አንቀጽ2(2) መሠረት ሰነዱ ማገቻ ስለሆነ የቴምብር ቀረጥ ይከፈልበታል ፡፡

**2.2.4** .**የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ** / ውል በጽሑፍ የሚደረግ ውል በመሆኑ በሰነዱ ላይ በሚፈጸመው ውል ምክንያት የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ የቴምብር ቀረጥ ይከፈልበታል፡፡

**2.2.5** . **ውል፣ ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ** ፤ -

በአዋጁ አንቀጽ 3 ሥር ከተዘረዘሩት የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች ውስጥ ውሎች ፤ ስምምነቶች እና መግለጫዎቻቸው በጽሑፍ በሚደረጉበት ጊዜ መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት ፤ የተመዘገበበት ወይም የተላለፈበት ወይም የተወገደበት እና የመሳሰሉት መብት እና ግዴታዎች የተመሠረቱበት ሰነድ በጽሑፍ ሲደረግ የቴምብር ቀረጥ ይከፈልበታል ፡፡

**2.2.6** . የመያዣ ሰነዶች ( ከባንክ ብድር ለመውሰድ መያዣ ሰነድ .....)

**2.2.7** . የህብረት ስምምነት

**2.2.8** . የሥራ ውል የተለየ የውል አደራረግ ባይኖረውም አሠሪው ከሠራተኛው ጋር የሥራ ውል በሚፈጽምበት ወቅት ሠራተኛው በውሉ መሠረት የተቀጠረበትን ጽሑፍ የመሥጠት ግዴታ ያለበት በመሆኑ የቅጥር ውሉ በጽሑፍ ቢደረግም ባይደረግም አሠሪው በሠራተኛው የቅጥር ፋይል ወይም መዝገብ መሠረት የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት ፡፡ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ **በቅጥር ውል** ላይ በአሠሪው ላይ የሚጣለው የቴምብር ቀረጥ በአግባቡ ሲሰበሰብ አይታይም ፤ ይህም ከታክሱ አስተዳደር አንጻር ሊታይ የሚገባውና **አሠሪዎች የሠራተኞቻቸውን የሥራ ግብር ሊከፍሉ በሚመጡበት ወቅት በቅጥር ውል ላይ የቴምብር ቀረጥ መከፈሉን ለማረጋገጥ ቢቻል** መንግስት ከዘርፉ ማግኘት ያለበትን ገቢ መሰብሰብ እንዲችል ያደርገዋል፡፡

2.2.9 . የኪራይ ፤የተከራይ አከራይ እና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ፤

2.2.10 ለማስረጃነት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው ሰነዶች የሚደራጁበትን እና የሚረጋገጡበትን አግባብ በፍትሐብሔር ህግ ከአንቀጽ 146 እስከ 153 ድረስ ተደንግጓል።

2.2.11 የውክልና ሥልጣን

2.2.12 የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ ናቸው ።

## 2.3. የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል

በሠነዶች ላይ የሚከፈል የቴምብር ቀረጥ የሚወሰነው ፣ የሚጠየቀውና የሚሰበሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው ።

| ተ.ቁ | የሠነዱ ዓይነት | የተወሰደ ስሌት መሠረት | የማስከፈያ ልክ |
|---|---|---|---|
| 1 | የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ማናቸውም ሌላ ማህበር የተመሰረተበት መተዳደሪያ ደንብ<br>ሀ/ መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ/ በመለጠቅ ሲፈጸም | <br><br>በቁርጥ<br>“ | <br><br>ብር 350<br>ብር 100 |
| 2 | የህብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ<br>ሀ/መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ/ በመለጠቅ ሲፈጸም | <br>በቁርጥ<br>“ | <br>ብር 35.0<br>ብር 10.0 |
| 3 | ግልግል | በዋጋው | የሚተመን 1%<br>የማይተመን ብር 35.00 |
| 4 | ማገቻ (ቦንድ) | በዋጋው | 1% |
| 5 | የዕቃ መከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ | በዋጋው | 1% |
| 6 | ውሎች ፣ ስምምነቶች ፣ መግለጫዎቻቸው | በቁጥር | ብር 5.00 |
| 7 | የመያዣ ሰነድ | በዋጋው | 1% |
| 8 | የህብረት ስምምነት<br>ሀ/ሲመዘገብ<br>ለ/ሲሻሻል | <br>በቁርጥ<br>“ | <br>ብር 350.00<br>ብር 100.00 |
| 9 | የቅጥር ውል ስምምነት | የአንድ ወር ደመወዝ | 1 % |
| 10 | ኪራይ ፣ የተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፍ ሰነድ | በዋጋው | 0.5 % |
| 11 | ማረጋገጫ | በቁርጥ | ብር 5.00 |
| 12 | የውክልና ሥልጣን | በቁርጥ | ብር 35 .00 |
| 13 | የንብረት ባለቤትነት ሥም ማስመዝገቢያ | በዋጋው | 2 % |

## 2.4. **የቴምብር ቀረጥ አተማመን፤**

በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን ከላይ በሰንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው የማስከፈያ ልክ ይሆናል ። ይኸውም የቀረጡ አተማመን **ሁለት** ዓይነት ስልትን የተከተለ ሲሆን የመጀመሪያው ስልት **በቁርጥ** የሚወሰን ሲሆን ይህም በሰነዱ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ በዋጋ ሊተመን የማይችል ሆኖ ሌለኛው የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በሰነዱ ላይ የሚፈጸመው መብት ወይም ግዴታ ወይም በሰነዱ ላይ የሚፈጸመውን **የግብይት ዋጋን** መሠረት ያደረገ በሰነዱ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው መብት ወይም ግዴታ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ሲሆን ቀረጡ በዋጋው መቶኛ ይወሰናል።

በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል ።

በአንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረት በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛ ልክ ነው ።

**በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ** ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሠረት ነው ።

ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በእያዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል

የንብረት ባለቤትነት ለማስመዝገብ በተቋቋመው ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በገቢ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኝ እንደሆነ እና በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ዋጋ የገቢ ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ በባለሥልጣኑ ይወሰናል

## 2.5. የክፍያ ግዴታ፡

- በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት ።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱን የሚሠረው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ ቀረጡን የመክፍል ግዴታ ሲኖርበት ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመው ሰው ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት።
- በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ተከራይ ቀረጡን ይከፍላል።
- በንብረት በለቤትነት ሥም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረት ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል ።
- ውል ወይም ስምምነት የሚመሰረቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።
- **በሥራ/ቅጥር ውል** ላይ የሚከፈለውን ቀረጥ የመክፈል ግደታ የአሠሪው ይሆናል ።
- **ጉዳያቸውን በግልግል** የሚያስወስኑ ወገኖች እና በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ ።
- በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሠሪውና ሠራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ ።

## 2.6. ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው ።

- **የንግድ ማህበር፤ የህብረት ሥራ ማህበር** ወይም ማንኛውም ዓይነት ማህበራት መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በመጀመሪያ ሲፈጸም እና በቀጣይ ሲፈጸም ወይም ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ ነው።
- **የህብረት ስምምነት ሰነድ** ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜ ሰነዱ ሲመዘገብ ነው።
- **በግልግል** (Award) **ሰነድ** ቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው ውሳኔው ከመሠጠቱ በፊት ወይም ውሳኔው በሚሠጥበት ጊዜ
- **የእቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ** ቀረጥ የሚከፈለው በሰነዱ ላይ ማረጋገጫ በሚሠጥበት ጊዜ ነው።
- **በማገቻ ሰነድ** ላይ የቀረጡ አተማመን በሰነዱ ላይ ባለው ዋጋ ልክ ነው። የሚከፈለው ሰነዱ በተፈረመበት ጊዜ ነው።
- **በውል ወይም ስምምነት** ሰነድ ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሠሪው ሆኖ ቀረጡን የመከፍያ ጊዜ የሥራ ውሉ በተደረገበት ጊዜ ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚርሙበት ጊዜ ወይም ከተፈረመ በኂላ ነው ። ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ተዋዋዮች በጋራ እና በተናጥል የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

- **ኪራይ፤ የተከራይ አከራይ እና መሰል የመብት ማስተላለፊያ ሰነዶች ላይ የቀረጥ** የመክፈያ ጊዜው ውሉ በሚፈረምበት ጊዜ ነው፡፡
- በንብረት ባለቤትነት ሥም ማስመዚገቢያ ሰነድ ላይ የመስመዝገቡ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸመምበት ጊዜ
- **የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ** ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜ የንብረት ባለቤትነት ስም የማስመዝገብ ተግባር ከመፈጸሙ ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ ነው፡፡
- **የውክልና ስልጣን ሰነድ** የቀረጥ አተማመን በቁርጥ ሲሆን የሚከፈልበት ጊዜም ውክልናው በሚሠጥበት ወቅት ነው፡፡
- የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50.00 በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ የሚፈጸም ሲሆን ከብር 50.00 የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ **የገቢዎች ሚ/ር በሚያወጣው መመሪያ** መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ በተለጠፈበት ሰነድ የሚሠራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሰራ መሠረዝ አለበት ፡፡
- ቴምብር የተለጠፈበት ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ የገቢዎች ባለሥልጣን በሚወስነው መሠረት ይፈጸማሉ ፡፡
- በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር የገቢዎች ባለሥልጣን በሚወስነው መሠረት ካልተሰረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል ፡፡ በዚህ ምክንያት የሚመጣው ኃለፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሠራ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል ፡፡

## 2.7. ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ስለመሆን

- በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች፤
- የአስመጪነት የንግድ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም ።
- መንግስት ባጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሠረት ሰነዶች ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ ።
- ተመሳሳይ መብት የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ኢምባሲዎችን ፤ ቆንስላዎችን እና ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን ገንዘብ ሚኒስቴር ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል
- የአይክስዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከተገልጋዮች ለገንዘብ ሚኒስቴር በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከቴምብር ቀረጥ ነጻ መሆን ይቻላል። በዚህም መሠረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥያቄዎች ቀርቦ ከቀረጡ ነጻ እንዲሆኑ የተፈቀዱ ሰነዶች /አገልግሎቶች ፡
- ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ሲባል በኢንቨስትመንት ህግ መሠረት ኢንቬስተር ተብሎ ዕውቅና የተሰጣቸው ባለሀብቶች ብቻ ለኢንቨስትመንት በሚወስዱ ብድር ጋር በተገናኘ በመያዣ ሰነድ ላይ ከሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ነጻ እንዲሆን በ19/02/97 በቁ. አመ3/21/44230 በተጻፈ ደብዳቤ በመመሪያ ተፈቅዷል ።
- የቴምብር ቀረጥ ህጉ በንብረት ባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የንብረቱ ዋጋ 2 % የቴምብር ቀረጥ እንዲከፈል የሚደነግግ በመሆኑ በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ንግድ ሥራ የተሰማሩ ድርጅቶች በኢንቨስትመንት ህጉ የሚፈቀዱ ንብረቶችን ለጥቃቅንና አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ዕቃዎችን በዱቤ ግዥ ሲያቀርቡ የሊዝ ጊዜው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ንብረቶች በአቅራቢው ድርጅት ሥም ስለሚመዘገቡ አቅራቢው ንብረቱ የሚገዛለት ኢንተርፕራይዝ ሥም በዕዳነት የሚመዘገብ የባሌቤትነት መመዝገቢያ 2% የቴምብር ቀረጥ መክፈል ያለበት ሲሆን የሊዝ ጊዜው ተጠናቆ ንብረቶቹ ሙሉ ለሙሉ ለኢንተርፕራይዞቹ እስከሚተላለፉበት ጊዜ ድረስ ከቀረጡ ነጻ ሲሆን ዕዳው ተጠቃሎ ሲከፈልና ንብረቱ ሲተላለፍላቸው ቀረጡን የሚከፍሉ ይሆናል ተብሎ የካቲት 20 ቀን 2009 ዓ.ም በቁ. ቴ/ቀ/7/89 በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያ ተላልፎ የነበረ ቢሆንም አዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ/ ለጥቃቅን፤ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞቹ በዱቤ ግዥ የሚያቀርባቸው የካፒታል ንብረቶች በስሙ ሲመዘገብ በባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ከሚከፈለው 2% የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነጻ እንዲሆን ስለመፈቀዱ በ20/11/2009 በቁጥር ቴ/ቀ/7//92 በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያ ተላልፏል ።

- በኤክስፖርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሥራ ማስከኛ ከሚወስዱት ብድር ጋር ተያይዞ በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ በምርት ዋጋ ላይ ውጤት እንዲኖረው በመጠቆም በ28/09/2007 ፤ በቁ.ቴ/ቀ/7/21 ቀን በተጻፈ ደብዳቤ ነጻ ተደርጓል ፡፡
- የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን ሴቶች በኢኮኖሚዊ ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ያላቸውን ተሳታፊነት በማሳደግ ረገድ ለሚያከናውነው ተግባር አቅም ለመፍጠር በገቢ ምንጭነት እንዲጠቀምባቸው ከመንግሥት የተሰጡት/የሚሰጡ ተሸከሪካሪዎች የባለቤትነት ሥም ዝውውር ሰነድ ላይ ስለሚከፈለው ቴምብር ቀረጥ በቀን 16 የካቲት 2007 ቁ.19/7/14/89 በተጻፈ ደብዳቤ ነጻ ተደርጓል ፡፡
- የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የማደበሪያ አቅርቦት ለአርሶ አደር ለማደል ከሚወስደው ሜርቸንዳይዝድ ብደር ጋር በተገናኘ በመያዣ ሰነድ ላይ ከሚከፈል በቀን 16/04/2007 በቁ. ቴ/ቀ/7/19 በተጻፈ ደብዳቤ ቴምብር ቀረጥ ነጻ ሆኗል ፡፡
- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለኢንተርፕራይዞች ለሊዝ ፋይናንስንግ ሥርዓት የሚያቀርባቸው ተሸከሪካሪዎች በባንኩ ንብረት ባሌቤትነት ሥም ማስመዝገቢያ ቴምብር ቀረጥ ነጻ እንደሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ በቁ.ቴ/ቀ/7/..በቀን 20/06/2009 በተላለፈ በሰርኩላር ፈቅዷል ፡፡

## 2.7. የቴምብር ቀረጥ ክፍያ አገልግሎት ተደራሽ ስለማድረግ

- ከተማ አስተዳደሮች/ክልሎች….ጥናቶችን በማካሄድ ከአንድ መስኮት አገልግሎት አሰጣጥ እና በመረጃ ምንጭ አስተማማኝነትና ውጤታማነት በመነሳት የቤት ባለቤትነት ሥም ዝውውር ሲከናወን በመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን
- ለነባር ተሸከሪካሪዎች በውልና የክብር መዝገብ አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል አገልግሎት እንዲሰጥበት በውክልና ተሰጥቶ እየተሠራበት ሲሆን
- ሌሎች ውሎችና ሰነዶች ላይ ግን የቴምብር ቀረጥ አዋጅ መሠረት ሰነዶችን በመመርመር የማስከፍል ሥራ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየክፍለ ከተሞች/ወረዳዎች ገቢ ጽ/ቤቶች የሚከናወን ሲሆን በክልሎች በየደረጃው ባሉት የገቢ ጽ/ቤቶች የሚፈጸም ነው ፡፡

የሙከራ ጥያቄዎች

1. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች አምስቱን ጥቀስ ፤
2. የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ምን ዓይነት ስልት ይከተላል ?
3. አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ( ቤት ) የተሸጠበት ዋጋ 7ሚሊዮን ብር ቢሆን የቴምብር ቀረጡ ስንት ይሆናል ?
4. ከቴምብር ቀረጥ ነጻ የሆኑትን ሶስት ግብይቶች / አገልግሎቶች ጥቀስ

## ክፍል ሶስት

# 3. ከቀረጡ ጋር ተያይዞ ስላለው አስተዳደራዊ ሁኔታዎችና ኃላፍነቶች

## 3.1. በቴምብር ቀረጥ ውሳኔ ላይ ስለሚቀረብ የቅሬታ ማስታወቂያ

- በባለሥልጣኑ ቀረጥ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔው ማሳታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በውሰኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ ታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በጹሑፍ ማቅረብ ይችላል ።
- ለባለሥልጣኑ ቅሬታ አቅርቦ በተሰጠው ታክስ ውሳኔ ላይ አሁንም በድጋሚ ቅር የተሰኘ ሰው ቅጣትና የዘገየ የከፍያ ወለድ ሳይጨምር በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶውን) በመክፈል ለግብር ይግባኝ ኮሚሽን በ30 (በሳላሳ) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል ።
- ኮሚሽኑም ባስተላለፈው ታክስ ውሳኔም ቅር ከተሰኘም የውሳኔውን 75% (ሰባ አምስት በመቶ) በመክፈል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል ።

## 3.2. አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች / ኃላፍነቶች

- **ከቴምብር ቀረጥ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች ማንኛውም ሰው ፤**
  - በምስክርነት ካልሆነ በስተቀር የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ሲገባ ቀረጡ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ያዋለ ወይም የፈረመ ወይም ፤
  - የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አነስተኛ የቴምብር ቀረጥ ለመክፈል በማሰብ የአንድን ሰነድ ትክክለኛ ባህርይ ያልገለጸ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከብር 25,000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) እስከ 50,000.00 ብር (ሀምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል ።
  - የቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ለመሸጥ የተፈቀደለት ሆኖ የቴምብር ቀረጥ አዋጁን ወይም ደንቡን የተላለፈ እንደሆነ ወይም ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሰጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ ብር 5,000.00 (ብር አምስት ሺህ ብር) እስከ ብር 25,000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ3-5 ዓመታት በሚደርስ ጽኑ ዕሥራት ይቀጣል ።

➢ **ይህ በእንዲህ እንዳለ ፤**

- የቴምብር ቀረጥ አለመክፈል የሚያስከትለው **ለሌኛው ውጤት** ማንኛውም ሰነድ በአዋጁ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በህግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፤ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም፤ በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን ግን አይመለከትም ፡፡
- በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ **በሁለት እጥፍ** ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ ፡፡ ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ10 ብር መብለጥ የለበትም ፡፡

የሙከራ ጥያቄ ፤

1. የቴምብር ቀረጥ በሰነዶች ላይ ለምን ይጣላል ?
2. በቴምብር ቀረጥ ውሳኔ ላይ ስለሚቀረብ ቅሬታ መስተንግዶን ግለጽ
3. በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች እንዴት ይስተናገዳሉ ?

**ማጠቃለያ**

የቴምብር ቀረጥ አንዱ የመንግስት የገቢ ምንጭ ከመሆኑም በላይ የቴምብር ቀረጥ የተለጠፈበት ሰነድ ለመረጃ/ማስረጃ ለመቅረብ ብቁ እንዲሆን የሚያስችል በመሆኑ ከዚህ ቀረጥ አኳያ ታክስ ከፋዮች ብሎም ሌሎች አካላት በቀረጥ አስተዳደሩ ላይ ግንዘቤ ይዞ የህግ ተገዥነት ደረጃቸውን ለማሳደግ ከቀረጡ ህግ ማዕቀፍ አኳያ ስለአሰራር ሥርዓቱ በሰነድ ተጠቃሎ ቀርቧል ፡፡

**<u>ማጣቀሻ</u>**


1. የቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954
2. ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 110/1990 ፤
3. የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻ የወጣ አዋጅ ቁጥር 612/2001
4. ፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁ.983 /2008
5. በገንዘብ ሚ/ር የተላለፉ ሠርኩላሮች ( በሰነዱ የተካተቱ )